# የልብ ጠጋኙ

## ማስታወሻ

በዶክተር ፈቀደ አግዋር



# የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ

በዶ/ር ፈቀደ አግዋር (2013 ዓ.ም)

ዶ/ር ፈቀደ አግዋር 2013 ዓ.ም

@ All rights are reserved.

የጸሀፊው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

የመጀመርያው እትም ነሀሴ 2013

ለአስተያየትዎ

ስልክ 0911 86 02 16

Telgram- Fekede Agwar

Instagram- Fekede Agwar

Email- kefedb@gmail.com

## ማውጫ

1. ሀፍረት እና ስኬት

2. አልፋ እና አሜጋዬ

3. አለምን ያስደመመው የልብ ውስጥ እጢ

4. ልብ እየመታ ልብ ሲጠገን

5. የሮይተርሱ ጋዜጠኛ

6. ታሪክ ባጋጣሚ

7. የመንታ ዘለላ

8. ጀግናዬ

9. ቤተሰብን ማከም

10. ደም መሸናትን ያስቆመው የልብ ቀዶ ጥገና

11. የሰማያዊ ህዓናት ህክምና በኢትዮጵያ

12. ላያስችል አይሰጥ

13. እትረፍ፡ ያለው

14. ውበት ሲፈነዳ

15. ቡናና ጊዮርጊስ በልብ ህክምና ሜዳ

16. ሞቱን ደገስኩለት

17. ሳማ ሰንበት

## ምስጋና፤

ከሁሉ አስቀድሜ ዛሬ ላይ በምክንያት ጠብቆ ላቆየኝ እና ከገጠሙኝ ክፉም ሆነ አስቸጋሪ ጊዜ አሳልፎ ለዚህ ቀን ያበቃኝ አምላክ ምስጋና ይግባው። በጥረቴ ሁሉ የፈጣሪ በረከት ባይኖረው ለዛሬው በረከትም ሆነ የገጠሙኝ ፈተናዎች ባላለፍኩኝ ነበር። ባስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ እና ደረጃ ውስጥም ሆናቹህ ለረጅሙ የኑሮዬ መስመር ከጎኔ የቆማችሁት ቤተሰቦቼስ፤ አቅማቹ በፈቀደ አሳድጋቹ ለዚህ አብቅታቹህኛልና ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቹ።

ለትምህርቴ እና ለስራዬ ስኬት ስትሉ የናንተን ምቾት ሰውታቹ መንገዴ እናዳይሰናከል፤ሲቀጥልም ሲደክመኝ እያበረታቹ አቅም ሳጣ አቅም የሆናቹኝ ባለቤቴ እና ልጆቼ በጣም እንደምወዳቹ እወቁልኝ። በተለይ ባለቤቴ መለይ መስፍን ቅዳሜ የለ እሁድ፤ ምሽት የለ ቀን፤ የአዘቦት የለ የባእል ቀን ሳልለይ ከቤት በምርቅበት የዘወትር ህይወቴ እንደ እናትም እንደ አባትም ሆነሽ ቤቴን መርተሻል። እየመራሽም

ነው። እንዳንቺ የሚረዳኝ ሚስት በማግኘቴ የሚሰማኝ ደስታ ወደር የለውም።

አንድ ልባቹን አምናቹ የሰጣቹኝ ታካሚዎቼ ለናንተ ያለኝ ቦታ ልዩ መሆኑን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ። ካለንበት የህክምና ደረጃ አንጻር፣ የልብ ቀዶ ጥገና ውስብስብነት እና ህክምናው የሚሰጠው ከውጭ በሚመጡ በጎ አድራጊዎች ለረጅም ዘመን ከመቆየቱ አንጻር የናንተን እምነት ማግኘት ከባዱ ፈተና ነበር። በሀገራችን የመጀመርያውም ሆነ ትልልቅ የልብ ቀዶ ጥገናዎችን በሀገራቹ ምድር እና በሀገር ቤት ሙሉ እውቀት እንዲሰራ የፈቀዳቹ ጀግናዎቻችን ናቹህ። በተገኘውም አመርቂ ውጤት እንኳን ደስ አላቹ። ፈጣሪ ቀሪ ዘመናቹን ይባርክ ዘንድ እመኛለሁ። በናንተ ምክንያት በተለኮሰው ሻማ ዛሬ የብዙዎች ህይወት መለወጥ የእለት ተእለት ክስተት ለመሆን ችሎዋል።

ዛሬም እንደሁሌው ከኔ ጎን ቆማቹ የዚህን መጽሀፍ የየራሳቹህን ታሪክ ለማንበብ ወይም ለመስማት ፍቃደኛ በመሆናቹ ደስ ብሎኛል። ከዚያም ባሻገር ገንቢ ሀሳብ ሰጥታቹ ታሪካቹን ስላዳበራቹት አመሰግናለሁ። ሲቀጥልም ስሜታቹህን በገዛ

ፈቃዳቹ ከታሪኩ መጨረሻ ላይ ስላሰፈራቹ ምስጋናዬ ክፍ ያለ ነው።

የልብ ማእከል በኢትዮጵያ በተለይም መስራች የሆኑት ዶ/ር በላይ አበጋዝ ዘላቂ መፍትሄ የሆነውን የሀገር ልጆችን እውቀት በልብ ቀዶ ጥገና ዙርያ ለማብቃት የዘመናት ትግል በመጨረሻም ፍሬ አፈራ። እኔም አንዱ የዚህ ትግል ፍሬ በመሆን ሙሉ በሙሉ የውጭ ዜጋ ድንበር የነበረውን የልብ ቀዶ ጥገና ሰብረን ገብተናል። ያለ ልብ ማእከል እና ያለ ዶ/ር በላይ አበጋዝ ህልም እራሴን እዚህ ቦታ ላይ ማሰብ ይከብደኛል። ልብ ማእከልም ካለበት ችግር ወጥቶ አብቦ እና ተስፋፍቶ ትልቅ የአፍሪካ የልብ ህክምና ማእከል እንዲሆን ምኞቴ ነው። ለዶ/ር በላይ አበጋዝም እረጅም እድሜና ጤና እመኛለሁ።

ይህችን አጭር ማስታወሻዬን ለመዓፍ እንድነሳሳ የመጀመርያውን ትልቅ ጉልበት የሆንከኝ እና ብርታትን ሰጥተህ ወደዚህ ሀሳብ ያስገባኸኝ እንደ ታላቅ ወንድሜ የማይህ ዶ/ር ስንታየሁ ዕጋዬ ይኸውልህ ምስጋናዬንም ስጦታዬንም ተቀበል። እንዲህም ሲል ነበር ያነሳሳኝ፤ የምርምር ፅሁፎችን እንደምትፅፍ አውቃለሁ ነገር ግን ይህንን አዲስ ድንበር

ከጀመርክ ጀምሮ በዙ ትልልቅ ስራዎች እንደሰራህ እናውቃለን። ታድያ ለምን እነዚህን ስራዎች ለምን ሰውኛ እና ተነባቢ በሆነ መልኩ ዕፈህ በታሪክ የማታስቀምጠው። ብሎ ነበር ውስጤ የነበረውን ስሜት እንዲለኮስ ያደረገው። በመቀጠል የስራ ባልደረባና ጓደኛዬ የሆንከው አቶ ሀይለሚካኤል ይሳቅ (ሀይልሻ) በየጊዜው ሞራሌ ዝቅ ሲል ከፍ እያረክ እበርትተኸኛል። ከቆምኩበት እንድራመድ ገፍተኸኛል። አመሰግንኸለሁ። እወድሀለሁ።

የተዝረከረከውን የወረቀት ዕሁፌን አክብረሽ የተቀበልሽኝ እና በተጣበበ የስራ ጊዜ እና ጫና ውስጥ ሆነሽ ጹሁፌን በኮምፒዩተር የከተብሽልኝ ማህደር ፈቀደ (ማሂ) ከልብ የመነጨ እና ወደር የሌለው ምስጋናዬን ተቀበይኝ።

እጅግ ብዙ ሩጫ በበዛበት በዚህ አለም ኑሮ የኔን የኑሮ ራስ ምታት ለማረም እና ለመምከር ጊዜያቹን የሰዋቹልኝ ውድ የሀገራችን ጉምቱ ጸሀፍያን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ተቀበሉኝ። በዚህ አጋጣሚ ለረጅም ጊዜ ሳከብርህ እና ሳደንቅህ የቆየሁት ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ ጹሁፌን ስለገመገምክልኝና እንድተዋወቅህ ስልፈቀድክልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። የዚህን መጽሀፍ ሽፋን ዲዛይን ለተጠበብክበት

ወንድሜ እና ጓደኛዬ አቶ ሳምኤል ሀይሉ (ሳሚ) አከብርሀለሁ፤ እወድሀለሁ፤ አመሰግንሀለሁ።

በመጨረሻም በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የልብ ቀዶ ጥገናዎች የተከናወኑበት ሶስቱን ሆስፒታሎች እና ሙሉ የስራ ባልደረቦቼን ከልዩ አክብሮት ጋር ለማመስገን እወዳለሁ።



## ስለ መፅሀፉ፡-

ይህ መፅሀፍ የተዋቀረው በአስራሰባት ታሪኮች ቢሆንም ፤ የመጨረሻዎቹ ሶስት ታሪኮች ግን የአንድ አላማ መዳረሻ ቅርንጫፎች ናቸው። ታድያ እነዚህ ታሪኮች ምንም እንኳን በልብወለድ መልክ ቢቀርቡም እውነት ከመሆንም ባሻገር በሀገራችን ልጆች እውቀት የልብ ቀዶ ጥገና እንዴት እንደተደፈረ፤ በመቀጠልም ትልልቅ የሚባሉ የልብ ቀዶ ጥገናዎች እንዴት እንደተጀመረ በትረካ መልክ ያቀርባል።

በመፅሀፉ ፍፃሜ ላይ እነዚሁ ታካሚዎች ያንን አስቸጋሪ ጊዜ አልፈው፤ ዛሬ ላይ ይህንን ጽሁፍ ባነበቡ ወቅት የተሰማቸውን ስሜት አስፍረነዋል። አሁን ያለውም ሆነ መጪው ትውልድ የልብ ቀዶ ጥገና ከውጭ ዜጎች ግዛትነት እንዴት ወደ ሀገር በቀል እውቀት እንደተሸጋገረ ቁልጭ አድርጎ ያመላክታል ብዬ እምናለሁ። ከሁሉም ባሻገር በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የሚንጸባረቁ ብዙ ስብዕናዎች ትውልድን ያነቃቃሉ፤ ያነጋግራሉ ብዬ አምናለሁ።

ፈቀደ አግዋር (የልብ ቀዶ ጥጋኝ)

ዋጋው፡
180 ብር (40 USD)

ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር
+251 111 565 352